# 6 መልእክት ለቤተክርስቲያን

## አስደናቂ ፈውስና ወደ ገነት ግብዣ ከእግዚአብሔር






**በ፡ ፓስተር ብራኒ ዱዮን**
(By: *Pastor Brani Duyon)*

*መግቢያ*

*በ ሜይ 2006 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) የእግዚአብሔር አገልጋይ ጌታ ኢየሱስን ለመገናኘትና 6 መልእክቶችን ለመቀበል ወደ ገነት ተወሰደ። ብራኒ ዱዮን በኤፈንዳይ (Efendie)፣ እድሜ 52፣ ከዱሰን (Dusun) ጎሳ። የሚያገለግለውም ኮታ ቤሉድ፥ ሳባህ (በምስራቅ ኢንዶኔዢያ) ቦርኒኦ (Borneo) ወንጌላውያን ቤተክርስቲያን ውስጥ እንደ ቤተክርስቲያን ሽማግሌ ነው። (Borneo Evangelic Church, Kota Belud, Sabah (in East Malaysia))። በሜላንግካፕ ባሩ፥ ኮታ ቤሉድ (Melangkap Baru, Kota Belud) በፓስተርነት (በመጋቢነት) አገልግሏል እንዲሁም በኋላ ላይ እ.ኤ.አ ከ2005-2006 ዓ.ም በኤስ.አይ.ቢ. ባያያት (SIB Bayayat) በቤተክርስቲያን አስተዳዳሪነት አገልግሏል።*



በአፕሪል 21፥ 2006 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) እኔና ባለቤቴ የልጃችንን ሠርግ ለመታደም ወደ ምእራብ ኢንዶኔዢያ አመራን። እንደ አለመታደል ሆኖ ከአንድ ሳምንት በኋላ፥ ራሴን ሳትኩ (stroke)። ወዲያውኑ ማላያ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ወደሚገኝ የህክምና ማእከል ተወሰድሁና በዚያ ሀኪሙ መረመሩኝ። በጭንቅላቴ ውስጥ የደም ቧንቧ መዘጋት ስላጋጠመኝ ባስቸኳይ ቀዶ ጥገና ማድረግ እንደሚገባኝ ነገረኝ።

ከቀዶ ጥገናው በኋላ ለአንድ ሳምንት ያህል በሰመመን ውስጥ ነበርሁ እናም ለአንድ ተጨማሪ ወር ደግሞ ከፍተኛ ክትትል እየተደረገልኝ ነበር።

የኤስ.አይ.ቢ. ሳባህ የቀድሞው ፕሬዚደንት፥ መጋቢ ቴፒን ሜሊዶይ (Pastor Taipin Melidoi)፣ ረዳቱ መጋቢ ዳቱክ አሩን ሰሉታን (Pastor Datuk Arun Selutan) እንዲሁም መጋቢ ሚካኤልን (Pastor Michael) ጨምሮ ሊጠይቁኝና ሊጸልዩልኝ የመጡ ብዙ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ነበሩ።

አንድ ጊዜ በህልሜ ከባድ ዝናብ ሲዘንብብኝ አይቼ ነበር። ይህንን ህልም እንዲሻለኝ ለጸለዩኝ መጋቢዎች የተሰጠ መልስ አድርጌ ተረጎምኩት። እግዚአብሔር ይመስገን፥ ከተጠበቀው ጊዜ አስቀድሞ ተሻለኝ።

አንድ ቀን እኩለ ሌሊት ላይ፥ በሜይ 2006 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) የመጀመሪያው ሳምንት፥ በጣም ለየት ያለ ስሜት ተሰማኝ። ሁሉም በሽተኞች ለጥ ብለው ሲተኙ እኔ ግን መተኛት አቃተኝ። በዚህ ሠዓት ሀሳቤ ኢየሱስ ላይ ብቻ ነበረ። በኢሳይያስ 43፥26 ላይ ያለውን አስታወስኩ "*አሳስበኝ፥ በአንድነትም ሆነን እንፋረድ፣ እንድትጸድቅ ነገርህን ተናገር።*" አእምሮዬ ሙሉ በሙሉ ጌታ ኢየሱስ ላይ እንዲያተኩር

ስለፈለግሁ እነዚህን ቃላቶች ማሰላሰሌን ቀጠልኩ። በዚያን ሠዓት የእግዚአብሔር በዚያ መኖር በኃይል ይሰማኝ ነበር።

ከዛም በመንፈስ መጸለይ ጀመርኩ። ከጸለይኩ በኋላ፥ ለመተኛት ሞከርኩ ግን አልቻልኩም። ከዛ አልጋው ውስጥ ወደ ኋላ ደገፍ አልኩ። በድንገት፥ ልክ የሆነ ሰው ጀርባዬን መታ መታ የሚያረገኝና ጭንቅላቴን የሚያሻሽኝ ዓይነት ተሰማኝ። ይህ ለጥቂት ጊዜ ሆነ። የሆነ የሚገርም ነገር ሰውነቴ ውስጥ ሲፈስ ተሰማኝ። አባት ለልጁ ያለው ፍቅር መሆኑን አመንኩ። ይህ ሰው ማን እንደሆነ ለማወቅ ጓጓሁ። ላየው ፊቴን ሳዞር፥ የሚያምር ወጣት ሰው በማየቴ ተገረምኩ፥ ጥሩ አቋም ያለው፥ ረዥም፥ እስከ ትከሻው የሚወርድ ረዥም ጸጉር ያለው። እናም ነጭ ቀሚስ ለብሶ ነበር። "*ሳስበው የነበርኩት ጌታ ነህ?*" ብዬ ጠየቅሁት፥ ጭንቅላቱን ብቻ አወዛወዘ። ከዛም በድጋሚ ጠየቅሁት "*ካልሆንክ ታዲያ አንተ ማነህ?*" በመጨረሻም ያናግረኝ ጀመር። "*እኔ ከሰማይ መልእክተኛ ነኝ። ኢየሱስ ወደ አንተ ለመልካም ዜና እንድመጣ ነገረኝ።*"

አሁን የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን አውቅሁ፥ ስለዚህም ጠየቅሁት "*ልትነግረኝ የፈለከው የምስራች ምንድ ነው?*" እርሱም መለሰ፤ "*ዛሬ ወደ ገነት ትሄዳለህ።*" ወዲያው ምንም ሰውነቴ ቢታመም መረጋጋትና ሰላም ተሰማኝ። ልክ እንዳልታመምኩ ያህል ተሰማኝ። መልአኩ ወደ ገነት እንደምሄድ በነገረኝ ቅጽበት ሙሉ በሙሉ ጤነኛ ሆንኩኝ። ከዛም ለመልአኩ እንዲህ አልኩት፤ "*ወደ ገነት ልከተልህ ዝግጁ ነኝ። ጌታዬን እስካየው ጓጉቻለሁ።*"

እየሄድን ሳለ ምድራዊ ሰውነቴ አልጋው ላይ እንደቀረ አየሁ። ልክ ከሀኪም ቤቱ እንደወጣን፥ የሚገርም ትልቅና ረዥም ፈረስ አየሁ። "*ይህን ፈረስ እንጋልባለን*" አለኝ መልአኩ። ፈረሱ በጣም ረዥም ስለነበረ መልአኩ ረድቶኝ ፈረሱ ላይ ወጣው። ከዛም መልአኩን ጠየቅሁት "*ይህን ፈረስ እየጋለብን ወደ ገነት መሄድ እንችላለን?*" መልአኩም መለሰልኝ፤ "*ያለ ጥርጥር፥ ሀሳብና ጭንቀት አይግባህ። ወደ ላይ ወደ ሰማይ ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ስለተወሰደው ስለ ኤልያስ የእግዚአብሔርን ቃል አንብበሀል?*" እኔም "*አዎ፥ ከዚህ በፊት አንብቤዋለሁ። በእሳት ፈረሶች በሚጎተት የእሳት ሰረገላ ነው የተወሰደው።*" አልኩት። መልአኩም፤ "*ትክክል ነው፥ አሁን የምንጋልበው ፈረስ ከእነዛ አንዱ ነው።*" አለኝ ።

በመጀመሪያ ፈረሱ ቀስ እያለ ይሄድ ነበር፥ ነገር ግን ከ100 ሜትር በኋላ ፈረሱ ተፈተለከ፥ በአውሎ ንፋስ (ሄሪኬን፣ hurricane) የተመታሁ ነው የመሰለኝ። ከዛም ሳይ ፈረሱ መብረር ጀምሯል። በእግዚአብሔር ኃይል እየበረርን ብዙ ተራሮችን በእርጋታ አለፍን።

ከዛ አረንጓዴ ሣር ያለበት ትልቅ ሜዳ ጋር ደረስን፥ ምንም እንከን የማይወጣለት ነበር፥ አንዲት ስንጣሪ የደረቀች ሣር እንኳን የለበትም። (መዝ.23:2 *በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።*) ፈረሱ ከቆመ በኋላ ወርደን በእግራችን መሄድ ጀመርን።

የእግዚአብሔር መንግሥት ፊት ለፊቴ ይታየኛል። በሜዳው ላይ እየሄድን ሳለ፥ ደወል ሲጮህ ሰማሁ። ከዛም መልአኩን ጠየቅሁት፤ "*ለምንድ ነው ደውል የሚጮኸው?*" እርሱም "*ደወሉ የሆነ ሰው የመምጣቱ ምልክት ነው።*" አለኝ።

ደወሉ ያለማቋረጥ እየጮኸ እያለ፥ እኛ ወደ ሜዳው ጫፍ መሄዳችንን ቀጠልን። በጣም የሚያምር ቤት አየሁ፥ በላዩ ላይ ቀይ መብራት አለ፥ ልክ እንደ ትራፊክ መብራት። በመብራቱ ላይ "51" ቁጥርን አየሁ። መልአኩን ቁጥሩ ምን ማለት እንደሆነ ጠየቅሁት። እርሱም "*አሁን እድሜህ ስንት ነው?*" አለኝ። በዚህ ሠዓት 51 ዓመቴ ነበር። መልአኩ "*ስለዚህ ያ ቁጥር እድሜህ ነው፥ እንዲሁም የቤት ቁጥርህ።*" ብሎ ነገረኝ። በእርሱ ለሚያምኑና ለሚከተሉት ልጆቹ አስቀድሞ በኢየሱስ የተዘጋጁ ብዙ ቤቶችን አየሁ።

ውስጡ ብዙ ሰዎች ወዳሉበት ግዙፍ ቤት መሄድ ቀጠልን። እግዚአብሔር የመረጣቸው ቅዱሳን ሰዎች እንደሆኑ አምናለሁ። እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር። ሁሉም ሰዎች እያመሰገኑትና እያመለኩት ኢየሱስ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ነበር። በፍጹም ልባቸው ያመሰግኑታል፥ ይዘፍናሉ/ ያሸበሽባሉ፣ እጆቻቸውን ወደ ላይ ያነሳሉ እናም በጉልበታቸው ይሰግዳሉ። በልቤ ጥልቀት እንዲህ አልኩ፤ "*በምድር ላይ ሰዎች እንደዚህ ቢያመሰግኑት እግዚአብሔር በጣም ይደሰት ነበር።*"

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔርን በሚያመሰግኑበት ሠዓት እንደሚያለቅሱ አየሁ። ኢየሱስም እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ እንዴት እንደሚተጉ እያየ ፈገግ ይላል። እጆቻቸውን ወደ ኢየሱስ ይዘረጋሉ፥ ኢየሱስም ሁሉንም ይባርካቸዋል። አገልግሎቱ ካለቀ በኋላ፥ ኢየሱስ በመካከላቸው ሄዶ እንባቸውን አበሰ። ከዛም በራእየ ዮሐንስ ላይ ያለውን ጥቅስ አስታወስኩ ራዕይ 21:4 "*እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው*

*ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም።*

መልአኩ ወደ ኢየሱስ አቀረበኝ። መልአኩም ለኢየሱስ እንዲህ አለው "*ጌታ ሆይ፥ ወደ እዚህ እንዲመጣ የመረጥኸው ልጅ ይህ ነው።*" ኢየሱስም እንዲህ አለኝ "*ግሩም! ልጄ ዛሬ መጥተሀል።*" ከዛም ኢየሱስ አቀፈኝ፥ በጣም ደስታና ሰላም ስለተሰማኝ አለቀስሁ። ነፍሴ በደስታ ዘለለች፥ ምክንያቱም ኢየሱስ ራሱ ስላቀፈኝ።

ከዛም መልአኩ እንዲህ አለ፤ "*ጌታ ሆይ፥ አሞት ሳለ በምድር ወደሚገኘው ቤቱ ሄድኩኝ፥ ሆኖም ግን አሁን ጤነኛ ነው።*" ጌታም መለሰ "*አዎን፥ በእርሱ የሆነውን ነገር አየሁ ሰማሁም።*" መልአኩም ቀጠለ "*በዚያን ሠዓት፥ ሚስቱ ያንተን እርዳታ ስትለምን ሰማኋት። እንዲህ እያለች ትጸልይ ነበር፤ 'ጌታ ሆይ እርዳን፥ እባክህ አሁን አትውሰደው ምክንያቱም እርሱ ይተወን ዘንድ ገና ዝግጁ አይደለንም።' ይህ ነበር ጸሎቷ ጌታ ሆይ።*" ከዛም ኢየሱስ እንዲህ አለ "*ሁሉንም አውቃለሁ። ሚስቱ እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ናት። ታማኝና ስትጸልይም ጽኑ ናት።*" የሚስቴን ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን እያሰብኩ ደግሞ እንደገና በነፍሴ አለቀስኩ።

ከዛም እግዚአብሔር ተናገረኝ፤ "*ልጄ፥ ወደ ምድር ተመልሰህ ትሄዳለህ ምክንያቱም በዚህ የመሆኛህ ሠዓት ገና አልደረሰም። ወደ እዚያ ስትመለስ ብዙ የምትሠራው ሥራ አለ። እኔን እያገለገልክ በሥራ ትጠመዳለህ።*" እኔም መለስኩኝ፤ "*ጌታ ሆይ፥ እባክህ ተመልሼ እንድሄድ አትጠይቀኝ ምክንያቱም እዚህ ከአንተ ጋር ስሆን በጣም ሰላማዊ ነኝ። ከአንተ አጠገብ ስሆን ደስታ ይሰማኛል ጌታ ሆይ። እባክህ፥ ተመልሼ መሄድ አልፈልግም።*"

ከፊቱ ላይ ኢየሱስ ቅር እንደተሰኘ ተረዳሁ። ስለዚህም ቅር አሰኘቼዋለሁና ይቅርታውን ለመንሁት። እንዲህ አልኩ፤ "*ጌታ ሆይ፥ ወደ ምድር ለመመለስ ዝግጁ ነኝ፥ ነገር ግን እባክህ እርዳኝ ጌታ ሆይ፥ ኃይልን ስጠኝ፥ በምሄድበት ሁሉ ተንከባከበኝ። ከእኔ ጋር ሁን ጌታ ሆይ።*" ከዛም ጌታ "*እሺ፥ አትፍራ፥ እኔን ለማገልገል በምትሄድበት ሁሉ እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ።*"

ኢየሱስ ወደ ምድር ይዤው የምመጣው መልእክት ነበረው። እነዚህን መልእክቶች በምድር ላሉ የእግዚአብሔር ልጆች እንድነግር ይፈልጋል። ኢየሱስ "*እነዚህ መልእክቶች በጣም ሊያውቋቸው የሚገባ እጅግ ጠቃሚ ናቸው።*" አለኝ። እነዚህን መልእክቶች በማውጣት (በመግለጥ) በጣም በሥራ እንደምወጠር ተነግሮኛል። እንዲሁም ኢየሱስ በገነት ያጋጠመኝን እንዲባረኩበትና እርሱን ለመከተል ኃይላቸውን እንዲያድሱ ለሁሉም የእግዚአብሔር ልጆች እንድነግር ነግሮኛል።

ኢየሱስ እንዲህ አለኝ፤ "*ወደ ምድር ስትመለስ እነዚህን መልእክቶች ለሁሉም ልጆቼ ንገራቸው።*" (***ኢየሱስ ለእኔ የሰጠኝ ስድስት መልእክታት ነበሩ።***)

## አንደኛው መልክት፡

"*ለልጆቼ፥ በፍጹም ልባቸው፣ በፍጹም ኃይላቸው፣ በፍጹም ሀሳባቸው እንዲያምኑኝ ንገራቸው። የሚፈሩ (የሚጨነቁ) ና የሚጠራጠሩ ወደዚህ አይገቡም።*" ይላል ጌታ ኢየሱስ።

## ሁለተኛው መልእክት፡

"*ለልጆቼ፥ ሁልጊዜም በታማኝነት ወደ ቤተክርስቲያን አገልግሎት (ጉባኤ) እንዲመጡ ንገራቸው፥ ምክንያቱም በመላ ገጻቸው ላይ የማበራበት ሠዓት ያ ነው፥ እነርሱም ፊቴን ይሹታል። ልጆቼን በቤተክርስቲያን ሲያመልኩኝ፣ ሲያመሰግኑኝ ሳይ በጣም እደሰታለሁ።*" ይላል ጌታ ኢየሱስ።

## ሦስተኛው መልእክት፡

“**ለልጆቼ፥ ሲጸልዩ፥ ፈቃዴን ሲያደርጉ፥ በቃሌ ሲኖሩ ታማኝ መሆን እንዳለባቸው ንገራቸው።**” ይላል ጌታ ኢየሱስ።

## አራተኛ መልእክት፡

“**ለልጆቼ፥አሥራትንና ምጽዋትን በመታዘዝ እንዲሰጡ ንገራቸው፥**” ይላል ጌታ ኢየሱስ።

(ኢየሱስ ይህን መልእክት እየሰጠኝ ሳለ፥እንዲህ አለኝ “**ልጄ፥ወደዚያ ተመልከት**” ለልጆቹ የተዘጋጁ የሚያማምሩ ቤቶችን አሳየኝ። “**ልጄ፥ እነዚህ ቤቶች ዝግጁ ናቸው፥ በእኔ ለሚያምኑና ለሚታዘዙኝ ልጆቼ ያዘጋጀሁት ነው።**” ከዛም ያላለቁ ቤቶችን አሳየኝ። “*ጌታ ሆይ፥ እነዚህ ቤቶች ያላለቁት ለምንድ ነው?*” ብዬ ጠየቅሁት። ጌታ ኢየሱስም እንዲህ አለኝ፣ “**ልጄ፥እነዚህ ቤቶች አሥራትና ምጽዋት ለመስጠት ለጋስ ያልሆኑ ልጆቼ ቤቶች ናቸው። እነዚህ ቤቶች ልጆቼ የበለጠ አሥራትና ምጽዋት በቤቴ ከሰጡ በኋላ አልቀው ዝግጁ ይሆናሉ።**”)

## አምስተኛ መልእክት፡

“**ለልጆቼ፥ በጸሎታቸው ሀብትና ንብረታቸውን ሁሉ በምድር እስካሉ ድረስ እንድጠብቅላቸውና እንድባርክላቸው ለእኔ እንዲሰጡኝ ንገራቸው፥ስለዚህም ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ምድር ስመጣ፥ ምድራዊ ሀብታቸው ላይ እንዳይጣበቁ። የሎጥን ሚስት ታሪክ አስታውስ፣**” ይላል ጌታ ኢየሱስ።

## ስድስተኛ መልእክት፡

“**ለልጆቼ፥ ዝግጁና ንቁ እንዲሆኑ ንገራቸው ምክንያቱም በቶሎ እመጣለሁና። ሰዎች ከሚገምቱት (ከሚጠብቁት) በቅርቡ!**” ይላል ጌታ ኢየሱስ።

(የኢየሱስ መምጫ አይታወቅም ነገር ግን መነጠቁ (ራፕቸር፣ rupture (1ተሰሎንቄ 4:15-18) ) በእርግጠኝነት ይሆናል። ጌታ ኢየሱስ በቶሎ ይመጣል!!!)

ኢየሱስ ስድስተኛውን መልእክት እየነገረኝ፥ ሰማዩን አሳየኝ፥ ጥርት ያለና ምንም ደመና ያልነበረበት ነበር። ኢየሱስ እጁን ወደ ምድር ከፍቶ እንዲህ ሲል አየሁት “***ልጆቼን ለመውሰድ ተዘጋጅቻለሁ።***” ከዛም ብዙ ሰዎች ነጭ ለብሰው ኢየሱስን ለመገናኘት ወደ ላይ ሲበሩ አየሁ። በኢየሱስ በግራውና በቀኙ በኩል ተሰብስበው ነበር። በኢየሱስ የሚያምኑ ብዙ ሰዎች ተነጥቀው ነበር። በተጨማሪም፥ የብዙ ቤተሰብ መላው አባል ሁሉ ሲነጠቅም አየሁ። ባልና ሚስት ከልጆቻቸው ጋር ወደ ኢየሱስ ሲበሩ አየሁ። ይህንን ትእይንት እያየሁ በጣም ሰላም ተሰማኝ።

ከዛም ጌታ ግድ አለኝ “**ወደታች ተመልከት።**” ከዛም ኢየሱስ በምድር ላይ ያለውን ሁኔታ አሳየኝ፥ የተመሰቃቀለ ነበር። በዚያ ሠዓት በምድር ላይ ምንም ሰላም አልነበረም። ሰዎች በየቦታው ሲሮጡና ሲጮኹ አየሁ። ወላጆች ልጆቻቸውን ሲፈልጉ እንዲሁም ወጣቶች ቤተሰቦቻቸውን ሲፈልጉ።

ኢየሱስ በእኔ ከተማ ያለውን ቤተክርስቲያን አሳየኝ። አንዳንድ ሰዎች ኋላ ቀርተው ሳይ በጣም ተከፋሁ።

ከዛም ኢየሱስ እንዲህ አለኝ “***ለእኔ ታማኝ ሁን። ያየኸውንና የሰማኸውን ሁሉ በምድር ላሉት ልጆቼ ሁሉ ልታስረዳቸው ይገባል።***”

ከዛም መልአኩ መጀመሪያ በሄድንበት ፈረስ መልሶ ወደ ምድር አመጣኝ። ምድር እጅግ በቶሎ ደረስን። ከዛም መልአኩ ወደ ሀኪም ቤቱ መልሶ ወሰደኝ። ልክ ምድራዊ ሰውነቴን እንዳየሁ መንፈሳዊ ሰውነቴ ወዲያው ተመልሶ ወደ እርሱ ገባ።

ሰውነቴ ከህመሜ ሙሉ በሙሉ እንደተፈወሰ ተረዳሁ። ስለ ኃይሉ እግዚአብሔር ይመስገን!

በገነት ሳለሁ ሰውነቴ ወጣት እንደነበርኩበት ጊዜ ይመስል እንደነበር አስታወስኩ።

ኢየሱስን በገነት ያየሁበት ምስክርነቴ ይህ ነው።



## በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን።

ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu Abdissa, matoughen@gmail.com